የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ግንቦት 20 2003

# ሕዝብን አስገድዶ ማሰለፍ የአምባገነኖች መለያ ነው

ህፍረተ ቢሱ የመለስ አገዛዝ ሕዝብ በገዛ ፍቃዱ ለግድብ መሥሪያ ገንዘብ እያዋጣ ነው ብሎ የቀባጠረው ያልበቃ ይመስል፤ 'በግንቦት 20 ሕዝብ በራሱ መዋጮና ኪሳራ ሊገነባ ነው የተባለውን የ80 ቢሊዮን ብር ግድብ ይሠራ ብሎ ደግፎ በብዙ መቶ ሺ ደረጃ ሊሰለፍ ነው' እያለ ሕዝብን ተሰለፉ አለበለዚያ ዋ በሚል ማስፈራራት መጀመሩ ሊታወቅ ተችሏል። ይህን ድርጊትና ዝግጅት ኢሕአፓ አጥብቆ ያወግዛል።

ሠፊው ሕዝብ በቅዳሜው ሰልፍ እንዲገኝ ጥሪ እየተደረገ ያለው በግንቦት 20 የወያኔ በዓል ስም ሳይሆን በግድቡ ግንባታ ስም መሆኑ የመለስን አገዛዝ ዕቅድና ግብ የሚሸፋፍን አይደለም። ለግብፅና ለዓለም ህብረተሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ የግድብ ግንባታውን (በዚያም ተያይዞ የመለስን አገዛዝ) እየደገፈ ነው የሚል መልዕክትን ወያኔ ለማስተላለፍ አቅዷል። በዚህም መሠረት የግዳጁን ሰልፍ የፍቃደኞች ሰልፍ ለማስደረግ እየተራወጠ ነው። የግዳጅ መዋጮን የፍላጎት መዋጮ አስመስሎ ለማቅረብ እየጣረ እንዳለው ሁሉ ማለት ነው። በወያኔ ሰልፍ ላይ አንገኝም ብሎ ዜጋ ሁሉ በየቤቱ እንዲቆይና በሰልፉ እንዳይገኝ ይጠበቃል። ግፊቱና ጫናው አይሎ በሰልፉም ቢገኝም ይህ ትርጉም ሚዛን አልባ መሆኑ ከወዲሁ መታወቅ ያለበት ነው። ግዳጅ ፍላጎትን ሳይሆን ፍርሀትን ገላጭ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የግዳጅ ሰልፍና መዋጮን በዘመነ ደርግ ያወቀውና በምፀትም የኖረው ነው። ዛሬም ገንዘብ ቢያዋጣ ሆነ ቢሰለፍ ተገዶ ነው። ይህን ግዴታ መቀበልን ግን እምቢ ማለት አለበት። አሻፈረኝ አላዋጣም፤ እምቢኝ አልሰለፍም ማለት ያሻዋል - የመጣውን ጭነትና መከራ ሁሉ መሸከም ግዳጁ አይደለምና።

ቅዳሜ ዜጎች ተገደውና አለውዴታቸው በወያኔ አጀንዳና መፈክር መሠረት ሰልፍ ቢወጡ አንደምታው ገለባ ነው። በማስገደድ እየተካሄደ ያለ ወያኔያው ትርዒት ነው። ሕዝብ ግን ለዚህ ሁሉ መሳሪያ መሆኔ ይብቃ ብሎ ማመፅና እምቢ ማለት ይጠበቅበታል። የወያኔ ሕዝብን የማስገደድ እርምጃ ግን ወያኔ ምን ያህል ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ዴሞክራሲ መሆኑን የሚያጋልጥ ነው። ቅሌቱና ህፍረቱ የወያኔ የራሱ ነው።

በወያኔ የተጠራውንም የግዴታ ሰልፍ ወደ ፀረ-ወያኔ ሰልፍ እንቀይረው!!
በመለስ አገዛዝ ላይ በጋራ እናምፅ!!

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com